| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ግጥም ፤ "ከመቃብር ፡ በላይ" ፡ ዐምድ ። |
| ርእስ ፤ | "እግዜር ፡ ያጥናሽ ፤ የሚበጀውን ፡ ይላክልሽ ። " |
| ደራሲ ፤ | መኰንን ፡ ተክለ ፡ አረጋዊ ። (†) |
| ዕለት ፤ | 1970 ዎቹ ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2011-002 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | (ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያልታተመ ። ) |

# ከመቃብር ፡ በላይ ።

## "እግዜር ፡ ያጥናሽ ፤
## የሚበጀውን ፡ ይላክልሽ ። "

መኰንን ፡ ተክለ ፡ አረጋዊ [1] ።

---

ሕዝብሽ ፡ እያነባ ፥ እንጀራ ፡ ተርቦ ፥
አካላዊ ፡ ኀይሉ ፡ በችጋር ፡ ተሰልቦ ፥
የምትሰጪው ፡ ዐጥተሽ ፥ የምታነጕቺለት ፥
የሚያጋድድ ፡ ታጥቶ ፥ የረባ ፡ ጎረቤት ፥
ዐይንሽ ፡ እንደ ፡ ናሴ ፡ እንደ ፡ ዋልካው ፡ መሬት ፥
በብካይ ፡ ተነድሎ ፥ ጨንቆሽ ፡ ብታነቢ ፥
ብትቅበዠበዢ ፥ ብትርገበገቢ ፥
ብትጣሪ ፡ አምርረሽ ፥ ብታረበርቢ ፥
መልካም ፡ ወዳጅ ፡ ዐጥተሽ ፥ የሚል ፡ እዚህ ፡ ግቢ ፥
ልቅሶሽም ፡ በርክቶ ፥ ሐዘንሽ ፡ ዐይሎ ፥
እየተጨናቈርሽ ፡ በዐይንሽ ፡ ጭገር ፡ በቅሎ ፥
ዋይታ ፡ በዝቶብሽ ፥ ተዘውትሮ ፡ ውሎ ።

እግዜር ፡ ያጥናሽ ፤
የሚበጀውን ፡ ይላክልሽ ።

አንጋፋ ፡ ልጆችሽ ፥ በኵሮችሽም ፡ ጠፍተው ፤
ይበልጦቹ ፡ እፊትሽ ፥ አጠገብሽ ፡ ታርደው ፤
ማሚጠጫዎቹ ፥
የኋላ ፡ ልጆችሽ ፥ ገና ፡ ማቲዎቹ ።
እያወኩ ፡ ባዝነው ፤
በውድማ ፡ ተረጭተው ፤
አረኽ ፡ ተንከራተው ፤
በዱር ፡ ተንቀዋለው ፤
ባላገር ፡ አጫርሰው ፤
ባህል ፡ አደፍርሰው ፤
እምነት ፡ አነውረው ።

በቄሎ ፡ ሲፈጩ ፤
ነድደው ፡ ሲቄላጩ ።

ውሃ ፡ ጠራርጓቸው ፥
ናዳ ፡ አውርዷቸው ፥
ድንጋይ ፡ ተጭኗቸው ፥
ወባው ፡ አንድዷቸው ፥
ችጋር ፡ ቈንድዷቸው ፥
በጥይት ፡ ተቈልተው ፥
በሹመት ፡ ተላልቀው ፥
ቀሪዎቹ ፡ አምልጠው ፥
ኹሉም ፡ ሙስሙስ ፡ ብለው ፥
መንምነው ፣ ገርጥተው ፥
ወቅዘው ፣ ሞግርረው ፥
ገቡ ፡ በሰው ፡ መንደር ፥
በማያውቁት ፡ አገር ።
ገረድ ፣ አሽከርነት ፡
ዐደሩ ፡ ሎሌነት ።

እግዜር ፡ ያጥናሽ ፤
የሚበጀውን ፡ ይላክልሽ ።

በዐምባሽ ፣ በከተማሽ ፣ በየወህኒ ፡ ቤቱ ፡
ታፍሰው ፡ የታጐሩ ፡ በየምክንያቱ ፥
እኽል ፡ ውሃ ፡ ሲሉሽ ፡ እንዲሁ ፡ የሞቱ ፤
አድኘን ፣ ታደጊን ፡ የዛሬን ፡ በብርቱ ።
ቢማጠኑሽ ፡ ጨንቆሽ ፡ ብትወናጨፊ ፥
ትኾኚውን ፡ ዐጥተሽ ፡ አብዝተሽ ፡ ብትለፊ ፥
ልቅሶሽ ፡ አድማጭ ፡ ዐጥቶ ፥ ከንቱ ፡ ኾኖ ፡ እሪታሽ ፥
ጨፍጭፈው ፣ ጨፍጭፈው ፡ በድን ፡ አስታቀፉሽ ፨

---

1 በ 1970 ዎቹ ፡ በሱዳን ፡ በረሓ ፡ በጠላት ፡ የተገደለ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የነጻነት ፡ ታጋይ ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።